# የወርቅ ኢዮቤልዩ እንዲህ አይከበርም ያለ ማነው?

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፐትርክና 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓል አከባበር በቤተ ክህነቱ ግቢ

*ምጥው ለቤ*

«የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ጵጵስና እና ፐትርክና ከግብጻውያኑ እጅ ተፈልቅቆ ወጥቶ በኢትዮጵያውያኑ ከተያዘ ወዲህ ለአገሪቱ ፈር ቀዳጅ የነበረው መልካም የአስተዳደር ፈሊጧ ጠፍቷል፣ አገርን አንድ አድርጎ ያኖረው አንድነቷ ተናግቷል፣ ከአስተዳደር መንበሯ የሚፈነጥቀው ቅድስናዋ ደብዝዟል» እያሉ በጠና የሚሞግቱ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ እንደ እነዚህ አበው አስተያዬት ቤተ ክርስቲያኗ ከመንበረ ማርቆስ ሙቀትና ክብካቤ ከቶዉኑም መለየት አልነበረባትም፡፡ ይልቅዬስ እንደ ጥንቱ መንበረ ፐትርክናዋ እስክንድርያ ኾኖ አስተዳደሯ ከዚያው ተመርጠው በሚመጡ ብፁዐን አበው እየተመራ መቀጠል ነበረበት ባዮች ናቸው፡፡ በአንጻሩ የሚያመዝነው የቤተ ክርስቲያኗ ሊቃውንት አስተያየት ደግሞ ያኛውን በጽኑ ያወግዛል፡፡ እነዚህኞቹ «ቤተ ክርስቲያኗ በጥምቀት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ወልዳ ዕውቀት መንፈሳዊን እየመገበች ያሳደገቻቸው የበቁ የተገ አባቶች እያሉ ምነው የአገሩን ቋንቋና ባሕል በማያውቁ ÷ ሕዝቡንም በቋንቋው እየባረኩ ማስተማር በማይችሉ «ባዕዳን» እየተመራች ትቀጥል?» ብለው ይከራከራሉ፡፡

በሁለቱም ገጽ ያሉት ሊቃውንት እንዳለመታደል ኾኖ በይፋ በተዘጋጀ ጉባኤ አቅርበው ባይከራከሩበትም በየምዕላዳቸው የሚሰጡት ምክንያት አለ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ቡድኖች ለክርክራቸው ግብ መምታት መጽሐፋዊና ታሪካዊ ምክንያት ይሰጣሉ፡፡ መጽሐፋዊው ምክንያታቸው ልዩ ልዩ ሥጋውያትና መንፈሳውያት የአስተዳደር ድንጋጌዎችን ከያዘው መጽሐፍ /ፍትሐ ነገሥት/ የሚጠ ቅሱት ነው፡፡ ያንን ጥቅስ እዚህ ልንጠቅስላቸው ግድ ይላል፡- «*ወሰብአ ኢትዮጵያ ኢይሚሙ ላዕሌሆሙ ሊቀ ጳጳሳት እማእምራኒሆሙ፤ ወኢበሥምረተ ርእሶሙ፡፡ እስመ ጳጳሶሙ ይከውን እምታሕተ እዴሁ ለበዓለ እስክንድርያ ወውእቱ ዘይደልዎ ይሚም ላዕሌሆሙ ሊቀ እምነቤሁ፤ ዘውእቱ መትሕተ ሊቀ ጳጳሳት፡፡* የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎቻቸው ወገን፣ በራሳቸውም ፈቃድ ሊቀ ጳጳሳትን ለራሳቸው አይሹሙ፡፡ ጳጳሳቸው ከእስክንድርያው በዓለ መንበር ሥልጣን በታች ነውና፡፡ ከሊቀ ጳጳሳት በታች የሆነውን ሊቀ ጳጳስ ከእርሱ ወገን ሊሾምላቸው የሚገባውም እርሱ ነው፡፡» (ፍትሐ ነገሥት፣ አንቀጽ 4፣ ቁጥር 50)

እነዚህ ቡድኖች ክርክራቸውን ጥግ ድረስ ለመውሰድ የሚጠቅሷቸው ሌሎችም መጽሐፋዊ ታሪኮች አሏቸው፡፡ ከላይኛው ተጨማሪ እንዲኾን የልዩ ልዩ ቅዱሳን ዜና ሕይወትና ተጋድሎ ከሚያትተው መጽሐፍ /ስንክሳር/ አንዱን ብቻ እንጥቀስ፡፡

*«በቅዱስ ሐርቤ ዘመነ መንግሥት አባ ሚካኤልም ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሁኖ በነበረበት ግዜ፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሐርቤ ለኢትዮጵያ አገሮች ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾም ዘንድ አባ ሚካኤልን አዘዘው፡፡ አባ ሚካኤልም ያለ ሊቀ ጳጳሳቱ ትእዛዝ ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም አልችልም ብሎ ለንጉሡ መለሰለት፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያ ንጉሥ ወደ አባ ገብርኤልና ወደ ግብፅ ንጉሥ እየለመነና እየማለደ ንጉሡ አባ ገብርኤልን እንዲአዝለት፤ አባ ገብርኤልም ለአባ ሚካኤል እንዲ ፈቅድለትና በተጨማሪ*

*ሌሎች ኤጲስ ቆጶሳትን አስቀድሞ በሾሟቸው ላይ እንዲሾም እንዲህ መልእክትን ላከ፡፡ የግብፅ ንጉሥም የኢትዮጵያን ንጉሥ ፈቃዱን ሁሉ ይፈጽምለት ዘንድ አባ ሚካኤል እንዲፈቅድለት አባ ገብርኤልን አዘዘው፡፡ ከዚህ በኋላ መኳንንቱ ወደ ግብፅ ንጉሥ ዘንድ ገብተው እንዲህ አሉት፡፡ በኢትዮጵያ ኤጲስ ቆጶሳት ቢበዙ ደፍረው ጳጳሳትን ይሾማሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ከቶ ወደ እኛ አይመጡም፡፡ ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲህ አዘዘው፡፡ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ አገር ኤጲስ ቆጶሳትን እንዳይሾም ለኢትዮጵያ ንጉሥ የውግዘት ደብዳቤ ላከ፡፡ ሊቀ ጳጳሳቱም የግብፅ ንጉሥ እንዳዘዘው ላከ፡፡ የውግዘት ደብደቤም ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ደርሳ በተነበበች ጊዜ የንጉሡ አዳራሽ ተቃጠለ፡፡ በኢትየጵያ አገርም ረኃብና ቸነፈር ሆነ፡፡ ዝናብም ተከለከለ፡፡ ችግርም ሆነ፡፡ የኢትየጵያ ንጉሥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎአልና፡፡ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ንጉሥ ተመልሶ ተጸጸተ፡፡ ወደ ግብፅም ይህን አባት አባ ገብርኤልን እንዲአዝለትና ከግዝቱ ይፈታው ዘንድ እየለመነ መልእክትን ላከ፡፡ የግብፅ ንጉሥም አዘዘለት፡፡ አባ ገብርኤልም የመፈቻና የቡራኬ ደብዳቤ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ እየባረከ ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ላከ፡፡ ይህች የበረከት ደብዳቤ ወደ ኢትዮጵያ አገር ደርሳ በተነበበች ጊዜ እግዚአብሔር መዓቱን ከላያቸው አርቆ ይቅርታውን ሰጣቸው፡፡ ዝናብም ወረደላቸው፡፡ ቸነፈርም ተወግዶ ታላቅ ደስታ ሆነ፡፡ ይህም በዘመኑ ሆነ፡፡»* /ስንክሳር፣ ሚያዝያ 10/

ከታሪክ አንጻር የሚሰጡት ምክንያት ደግሞ 13ኛውን መቶ ክፍለ ዘመን ከ20ኛው ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡ በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንድ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ አባት «ጵጵስና የግድ ለመንበረ ማርቆስ» ለሚሉቱ እንደ መከራከሪያ ነጥብ የሚቀርብ ተግባር ፈጽመዋል፡፡ ነገሩም እንዲህ ነው፡- በዓለም ታሪክ ተመዝግቦ እንደ ሚገኘው እ.ኤ.አ. ከ1095 - 1291 ክርስትና አብባ ፍሬ መስጠት የጀመረችበት የላቲኑ ዓለም በወቅቱ በነበረው ፓፓ አዝማችነት ቅድስት አገር ኢየሩሳሌምን ከመሐመዳውያን ቁጥጥር ነጻ ለማድረግና አካባቢውንም በኃይል ክርስትናን እንዲቀበል በማድረግ ጦርነት አውጆ ነበር፡፡ በጦርነቱ የተነሳ እንደተለመደው ኢትዮጵያን የሚመራት አባት ከእስክንድርያ መምጣት አልቻለም ነበር፡፡ በወቅቱ በቅድስናቸውና በአስተዳደራቸው አንቱ የተባሉትና የደብረ ሊባኖስ እጨጌ የነበሩት ኢትዮጵያዊው ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መንበረ ጵጵስናውን እንዲይዙ ተደርጎ ነበር፡፡ ኢትዮጵያዊው ጻድቅም ተወልደው ባደጉበት ሕዝብ መካከል ተግተው በታሪክ ሲዘከሩ የሚኖሩ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ሰጥተዋል፡፡ ቃለ እግዚአብሔር ያልሰማው ሕዝብ እንዲሰማ ሐዋርያት በዓለም ዙሪያ ወንጌልን ለመስበክ እንዳደረጉት ከደቀ መዛሙርታቸው የበቁትን መልምለው ኢትዮጵያን አከፋፍለው ለስብከት አሰማርተዋል፡፡ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደርም እንዲጠናከር፣ ገዳማቱና አብነት ት/ቤቶቹ እንዲስፉፉ አድርገዋል፡፡ ካህናትን ሹመዋል፡፡

መካከለኛው ምስራቅን ለረጅም ጊዜ ሲያውክ የነበረው የመስቀል ጦርነት ተጠናቆ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተለመደው ከልጆቿ መርጣ አንዱን ወደ ርስት አገሯ ኢትዮጵያ ስትልክ በመንፈሳዊ ሕይወት ብስለታቸው በአስተዳደር ብቃታቸው የተመሰከረላቸው ጻድቅ አባት አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ይሁኑ በወቅቱ ያንን ያዩ ሊቃውንት «አንፈልግም፤ ራሳችንን በራሳችን እናስተዳድራለን፤ እንግዲህስ ይበቃናል» ሳይሉ የመጡትን አባት በክብር ተቀብለው መንበሩን አስረክበዋል፡፡

ስለዚህ የመጀመሪያዎቹ ተከራካሪዎች ይኸንን የ13ኛው መ.ክ.ዘ. ታሪክ በ20ኛው መ.ክ.ዘ. ኢትዮጵያውያን አበው ከተሾሙበት ጊዜ ጀምሮ የተፈጠሩ አሉታዊ አስተዳደራዊና መንፈሳዊ

ችግሮች ጋር እያገናኙ ይሞግታሉ። የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ እግዜሩ ቢፈቅድለት የቤተ ክርስቲያኗ ጵጵስናም ኾነ ፐትርክና በኢትዮጵያውያኑ አባቶች ከተያዘ ወዲህ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመዳሰስ ይሞክራል።

ከላይኞቹ አንጻር ቆመው የሚከራከሩት የሚያቀርቡት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያኗ የታሪክ ውቅያኖስ የሚቀዳ ነው። ላይኞቹ የሚጠቅሷቸውን መጽሐፋዊ ምክንያቶች «ግብጾቹ የአስተዳደር ቀንበራቸውን ሊያጠብቁብን በአዋልድ መጻሕፍቱ የጨመሯቸው «ስርዋጽ» » ብለው ውድቅ ያደርጓቸውና፣ የቤተ ክርስቲያኗን አስተዳደር ከግብጾች እጅ ፈልቅቆ ለመውሰድ ኢትዮጵያውያን ነገሥታትና ሊቃውንት በየዘመኑ ያደረጓቸውን እልኽ አስጨራሽ ትግሎችና የተገኘውን ድል በኩራት ይጠቅሳሉ።

እስካሁን ባሉ መረጃዎች በ4ኛው መ.ክ.ዘ በአቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ተጀምሮ ለረጅም ጊዜ የቆየውን «የግብጽ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ቅኝ ግዛት» ለመጀመሪያ ጊዜ በመቃወም ኢትዮጵያውያን አበው ኤጲስ ቆጶሳት ኾነው ይሾሙ ዘንድ ድምጹን ያሰማው በቤተ ክርስቲያኗ ቅዱሳን ተብለው ከተመዘገቡ አበው አንዱ የኾነው ንጉሥ ሐርቤይ /1060 – 1077 ዓ.ም/ ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ማርያም ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በየዘመኑ የነገሡ ነገሥታትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያንኑ ጥያቄ እያነሱ ከመንበረ ማርቆስ ተሹመው የሚመጡ ጳጳሳትን ሲሞግቱ ቆይተዋል። ለእነዚህኞቹ መንበረ ጵጵስና ወፐትርክናው በግብጾቹ ተይዞ በመቆየቱ ቤተ ክርስቲያኗ ካገኘችው ያጣችው ይበዛል። ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት አገሪቱንና አካባቢዋን ከአረማውያንና እስማኤላውያን ጥቃት አልታደጉም፣ ለእነሱ እጅ መንሻና መማለጃ የቤተ ክርስቲያኒቱ በእሷም በኩል የአገሪቱ ሀብትና ንብረት ባክኗል፣ አስተዳደር ባለመቻላቸው በየዘመኑ ቤተ ክርስቲያኗ በልዩ ልዩ ውስጣዊ የነገረ ሃይማኖትና አስተዳደራዊ ክፍፍሎች እንዲሁም ግጭቶች እንድትታመስ አድርገዋል፣ እነሱ ከፊት ቆመው መንገድ በመዝጋት ኢትዮጵያውያኑ ሊቃውንትና ቅዱሳን በዘመናቸው ለአገራቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ጠቃሚ ሥራ ሳይሠሩ እንዲያልፉ አድርገዋቸዋል፣ አገሪቱ በጠላት እጅ ሥር ስትወድቅ ሕዝቡንና ቤተ ክርስቲያኗን ለጠላት ትተው ወደ አገራቸው ሔደዋል ወ.ዘ.ተ. የሚሉ ወቀሳዎችን ደርድረው እራሳችንን በራሳችን ማስተዳደር በመቻላችን ቤተ ክርስቲያናችን አድጋለች ይላሉ።

በእውነቱ የክርክር ገመዱ በዬትም ያዝምም በዬት ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዬትኛውም የውጭ አስተዳደር ነጻ ኾና፣ መናብርተ ጵጵስናዋም ይሁኑ ፐትርክናው በራሷ ልጆች ተይዘው «ራሷን በራሷ» እየመራች ትገኛለች። እንደውም አክርሞን ሊሰናበተን ውኃውን ማፍሰስ ብቻ የቀረው 2001 ዓ.ም ይህ አስተዳደራዊ ነጻነት በከፊልና ሙሉ በሙሉ የተረጋገጡበት ወርቃማ የታሪክ አንጓዎች ምክንያታዊ በኾነ መልኩ የሚዘከሩበት ዓመት ነው። እሱም ብቻ አይደለም፣ (ከላይ ከነክርክራቸው ቢጋር ካቀርብኳቸው ቡድኖች የትኞቹን ያስደንግጥ ዬትኞቹን ጥርስ ያስነክስ ባላውቅም) ከመሰንበቻው ከጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ግቢ ቱር ብሎ እየጓነ በመፈንዳት የቤተ ክርስቲያኗን ልጆች እያሸበረን ያለው ዜና መፈንዳት የጀመረበት ያለፈው የግንቦትና ፍንዳታ ተጋግሎ የቀጠለበት እየተገባደደ ያለው የሰኔ ወራት፣ አበው ለ1600 ዓመታት የተጋደሉለት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ነጻነት ትግል በከፊልና ሙሉ በሙሉ ድል ያስመዘገበባቸው 80ኛና 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዩቤልዩ መታሰቢያ ወራት ናቸው።

በቤተ ክርስቲያኗ የታሪክ መዝገብ ጵጵስናን በሚመለከተው ምእራፍ እንደ ሰፈረው ግብጾቹ መልካም ፈቃዳቸው ኾኖ ለመጀመሪያ ጊዜ አራቱ ኢትዮጵያውያን አበው [መምህር ደስታ (አቡነ አብርሃም)፣

መምህር ኃይለ ማርያም ÷ (አቡነ ጴጥሮስ)፣ መምህር ወልደ ኪዳን ÷ (አቡነ ይስሐቅ)፣ መምህር ኃይለ ሚካኤል ÷ (አቡነ ሚካኤል)] «ይደልዎ» ተብለው ኤጲስ ቆጶስነት የተሾሙት ግንቦት 25 ቀን 1921 ዓ.ም ነበር፡፡ ዘንድሮ 80ኛ ዓመቱ፡፡ ኢትዮጵያ በፋሺስት እሳት ስትጋመድ ባዕታቸውን ወደ ግብጽ አዙረው እሳቱ የፈጀውን ፈጅቶ ሲጠፋ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት የመጨረሻው ግብጻዊ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በሞተ ሥጋ አስገዳጅነት መንበሩን ሲለቁ /መንበረ ሊቀ ጵጵስናውን/ በ1943 ዓ.ም ተረክባ ስታበቃ፣ ቤተ ክርስቲያኗ ሰኔ 21 ቀን 1951 ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነቷ ግቢ መንበረ ፓትርክናዋን ሠርታ የራሷን ልጅ በመሾም ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ግዞት ሙሉ በሙሉ ነጻ ኾነች፡፡ ልክ 50ኛ ዓመቱ፡፡

ታዲያ ከእግዚአብሔር በታች ቤተ ክርስቲያኗን እንዲመራ ሥልጣን የተረከበው ቅዱስ ሲኖዶስ ለዛሬ ሕልውናው መሠረት የኾኑትን እነዚህን በዓላት ሳያስበው በኾነው መልኩ እያከበራቸው እንደኾነ ይስተዋላል፡፡ በኾነው መልኩ ሲባል አንድም ሲኖዶሱ እየተገባደደ ያለው ዓመት ከላይ የተጠቀሱት ዐበይት ድሎች የሚወሱበት መኾኑን የዘነጋው፣ ምናልባት አስታውሶትም ከኾነ ሊያከብረው ግድ የሌለው ስለ ሚመስል (የአንድን ግለሰብ ልደት ወይም የሹመት በዓል ለማክበር ቀሚሱን እየገተተ ገንዘብ ሲመዝርጥ ወገቡ እስኪንቀጠቀጥ ቆሞ ሲያወድስ የምናየው ሲኖዶስ ይኽንን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ነጻነት የተረጋገጠበትን በዓል ለማክበር በግልጽም በስውርም ለማክበር ሲንቀሳቀስ አላየንም አልሰማንምና )፣ አንድም ብዙ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ዐበይት የመታሰቢያ በዓላት /ያውም መንፈሳውያት/ በሚከበሩበት መልኩ ሳይኾን በራሱ አስተዳደር እንቅስቃሴ ካለመርካት በመጣ ክርክርና ጉትቻ እያከበረው ስለሚመስል ነው፡፡ የኾነ ጉዳይ 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዩቤልዩ በዓል ብዙ ታስቦ ተደግሶለት ሰፋ ያለ እድምተኛ ተጋብዞ በደስታ ሲከበር እያየ ለኖረ ሕዝብ «ጥላቻና ጉትቻ ምን በዓል ማክበር ነው?» ቢል የሚገርም አይኾንም፡፡ ነገር ግን ለዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እነዚያ በዓላት እየተከበሩ ነው፡፡ ይህንን የሚለው እየተስተዋለ ያለው የእርግጫና ቱጫ በዓል አከባበር ለቤተ ክርስቲያኗ የነገ እርምጃ መንገድ ይጠርጋል፣ በዚህም በያለንበት ኾነን የቤተ ክርስቲያናችንን አስተዳደራዊ ብልዬት እያየን አንገታችንን ያስደፋንን ሁሉ ቀና ያደርገናል ከሚል ነው፡፡

እንደተሰማው ባለፈው ግንቦት (የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያን አበው ሥልጣነ ኤጲስ ቆጶስነትን በተረከቡበት ወር ልክ 80ኛ ዓመት ላይ) ተደርጎ በነበረው መደበኛ ጉባኤ ላይ በጠትርያርኩና የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደራዊ ጉዞ መንገዱን ስቷል ይስተካከል ባሉ ሊቃነ ጳጳሳት መካከል ሞቅ ያለ እሰጥ አገባ ተነሥቶ ነበር፡፡ እሰጥ አገባው እንደገና የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጠትርያርክ ከፍ ባለ መንፈሳዊ ደስታ የተመረጡበት የሰኔ ወር 50ኛ ዓመት ከመጠናቀቁ በፊት ምናልባት በየወሩ ሲሰበሰብ የመጀመሪያ በኾነ መልኩ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም አስቸኳይ ምልአተ ጉባኤ እንዲጠራ ኾኗል፡፡ ኃላፊነት ያለባቸው ሊቃነ ጳጳሳትም ለዚሁ ታላቅ ጉባኤ ከየሀገረ ስብከታቸው ወደ መንበረ ጠትርያርኩ እየተሰበሰቡ ነው፡፡ በፍንዳታው እየተረበሽን ያለን የቤተ ክርስቲያን ልጆችም ይህ ወሳኝ ጉባኤ አንገታችንን ላስደፉን በርካታ አስተዳደራዊ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል ብለን ውጤቱን በጉጉት እየጠበቅን ነው፡፡

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ የጉባኤው ሒደትና ውጤት የሚከተሉት እንዲኾኑ ይመኛል፡፡ ወዲያውም መልእክቱን ያስተላልፋል፡፡

1. የዚህ ቅዱስ ጉባኤ አባላት /ብፁዐን አበው/ ከእንካ ሰላትያ ርቀው የቤተ ክርስቲያኗን ልጆች በሀፍረት አንገታችንን ያስደፉ ልቡናችንን ሲበዘብዙ የሚኖሩ መሠረታዊ ችግሮች ላይ ተወያይተው በመንፈሳዊ ሐሴት እግዚአብሔርን እንድናመሰግን እነሱንም እንድናከብራቸው የሚያደርጉ ውሳኔዎችን በጉጉት እንደምንጠብቅ እንዲረዱ፤ እንደ ተለመደው በኮሚቴ ይጠና ብላችሁ እንዳትቀብሩትና እንዳትቀብሩን፤
2. ሊቃነ ጳጳሳቱ ቤተ ክርስቲያናቸው ሥልጣኑን የሰጠቻቸው ከውስጣዊ ምዝበራና ከውጫዊ ውርወራ እንዲጠብቋት መኾኑን ተገንዝበው ያለምንም ፍርሐትና አድር ባይነት ቀረቡ በተባሉትም ኾነ እነሱ በየማስታወሻቸው በያዟቸው ወቅታዊ የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ዙሪያ እንዲከራከሩ
3. ጉባኤው በቤተ ክርስቲያኗ መሠረታዊ የአስተዳደር ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ ሲሰጥና ቤተ ክርስቲያኗ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን ያረጋገጠ አስተዳደራዊ ስልት ስትዘረጋ የጥቅም ጉሮሮአችን ተዘጋ ብለው የሚጮኹ ውሾች በቤተ ክህነቱ ውድማ እንደሚኖሩ አውቀው እዚያ ወርቃማ ውሳኔ ላይ እንዳይደርሱ በግልጽና በስውር የሚያቀብሏቸውን የሐሳብ ተዋሕስያን ይዘው ወደ ተቀደሰው ጉባኤ እንዳይገቡ፤ የሽጉጥ ማስፈራሪያቸውንም ከቁብ እንዳይቆጥሩ፤
4. ውይይታቸውና ውሳኔያቸው ሁሉ የነገውን የቤተ ክርስቲያን ጉዞ የሚያስተካክል እንጂ የትላንትን ስሕተት የሚደግም ወይም ምክንያት የሚሰጥ እንዳይኾን፤
5. የአገሩ መንግሥት ከቤተ ክህነቱ ቅጽር ግቢ ተስፈንጥሮ ወደ ላይ ጉኖ ሲያበቃ የሚነጉደውን ዜና አልሰማም ማለት ጅልነት ስለሚኾን በግልጽም ይሁን በስውር በጉባኤው ላይ እጁን እንዳያሳርፍ፤ ለአባቶቻችን ነጻነት እንዲሰጥ፤
6. ምእመናን አሁን ያሉት ሊቃነ ጳጳሳት ያገለግሉን ዘንድ እግዚአብሔር የሾመልን አገልጋዮቻችን እንጂ የቤተ ክርስቲያኗ ባለቤቶች እኛ መኾናችንን ተረድተን ጉዳዩን በጥንቃቄ እንድንከታተለውና ነገ እናገኘው ዘንድ ለምንፈልገው የእናት ቤተ ክርስቲያናችን ሙቀት እውንነት አባቶቻችን በጥንካሬ ተወያይተውና ተከራክረው ጠቃሚ ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ በያለንበት ግፊት እንድናደርግ፤
7. የቤተ ክርስቲያኗን የነገ ጉዞ የተቃና እንዲኾን ከልብ የሚመኙና ለዚያም በትጋት የሚሠሩ ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ማኅበራት ቤተ ክርስቲያን ከተጣባት የአስተዳደር ደዌ የምትፈወስበት ጊዜው አሁን መኾኑን ተረድተው እውነት እንድታሸንፍ የቻሉትን ያህል እንዲያደርጉ፤

ያ የኾነ ጊዜ ጵጵስና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት 80ኛ ዓመት ቤተ ክርስቲያኗ መንበረ ፓትርክናዋን አደላድለ ከልጆቿ መርጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስቀመጠችበት 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዩቤልዩ በዓል ተከበረ እንላለን፡፡ ይህችን አጭር መጣጥፍ ሳዘጋጅ በተለይ የጵጵስናን የሽግግር ታሪክ በሚመለከት ዲ.ን መርሻ አለኸኝ የተባሉ ሰው «ዜና ጳጳሳት» በሚል አሳትመው ያቀረቡልን መጽሐፍ በዋና ምንጭነት አገልግሎኛልና ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ ቸር ወሬ ያሰማን፡፡